ספריית פיג'מה






በ: ባርባራ ብራውን
ምሳሌዎች: ስቴሲ ሾት
הוֹצָאָה: ידיעות ספרים
የእድሜ ክልል: አንደኛ ክፍል

שִׂיחָה

**ውይይት– ሐኑካችን**

የሐኑካ በዓል በዓለም ዙሪያ ባሉ አይሁዶች በትውልዶች ሁሉ ይከበራል። በበዓል ወቅት ስለ ቤተሰብዎ ወጎች ማውራት ይችላሉ – ምን ዓይነት ልማዶች አሉዎት? በአላስካ ካሉ የሐኑካ ልማዶች ጋር እንዴት ይመሣሠላሉ? ?ባልተለመደ ሁኔታ ወይም ልዩ ቦታ ላይ አክብረው ያውቃሉ

לָצֵאת הַחוּצָה

**ከውጪ ባለ ብርሃን - ከውስጥ ባለ ብርሃን**

በታሪኩ ተመስጦ ምሽት ላይ መውጣትና በዙሪያዎ ያሉትን ብርሃኖች ማየት ይችላሉ፡- ኮከቦችን፣ ጨረቃን፣ የመንገድ መብራቶችንና ምናልባትም የሐኑኪያ መብራቶችን ይመልከቱ – ምን ያህል መብራቶችን ይመለከታሉ? ውጪ ለምታገኟቸው እያንዳንዱ የብርሃን ምንጭ የሚያስደስትዎ፣ የሚያበረታዎ ወይም ለሕይወትዎ ብርሃንን የሚያመጣ ነገር ላይ መናገር ይችላሉ።

מִשְׂחָק

**ሐኑካ በዓለም በሁሉም ቦታ**

ዛሬ ሻማዎችን የት ማብራት ይፈልጋሉ? በእሥራኤል ውስጥ ልዩ ቦታ ላይ? በሰሃራ በረሃ? ወይስ ምናልባት በበረዷማዋ አላስካ ውስጥ? በየእለቱ በተለየ ቦታ እያከበሩ እንደሆነ የሚያስቡበት የዓለም ካርታ መስራትና አስደሳች ጨዋታ መጫወት ይችላሉ! በዙሪያዎ ያለው ምንድን ነው? ከፓንኬኮችና ዶናት በተጨማሪ ምን ይበላሉ? በበዓሉ ላይ ?ምን ዓይነት የሀገር ውስጥ ልማዶችን ይጨምራሉ

יְצִירָה

**ሰሜናዊው ብርሃን**

የመጽሐፉን ምሥሎች በመመልከት በማርከሮችና በባለቀለም እርሳሶች አንድ ላይ ለመሳል መነሳሳትና የራስዎን አስደናቂ የሰሜናዊ ብርሃንን መፍጠር ይችላሉ።

שְׁמַע

**QR ኮድ**

ስለ ሰሜናዊ ብርሃን ክስተት የበለጠ ማወቅ ይፈልጋሉ? ኮዱን ስካን ያድርጉና ስለ አስደናቂው የሰሜናዊ ብርሃን ቪዲዮ ይመልከቱ።

הַשְׁרָאָה

**ፒንተረስት**

[ተጨማሪ ስራዎችን፣ ግጥሞችንና እንቅስቃሴዎችን በፒጃማ ቤተ መፃህፍት ፒንተረስት ላይ]

עוד פעילויות באתר ספריית פיג'מה www.pjisrael.org